Ministry of justice

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ

FEDERAL NEGARIT GAZETA

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

አሥራአምስተኛ ዓመት ቁጥር ፶
አዲስ አበባ ሐምሌ ፫ ቀን ፪ሺ፩ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

15th Year No. 50
ADDIS ABABA 10th July, 2009

ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፮፻፵፬/፪ሺ፩ ዓ.ም

ከስፔን ንጉሣዊ መንግሥት ጋር ኢንቨስትመንትን ለማስፋፋትና ዋስትና ለመስጠት የተደረገውን ስምምነት ማጽደቂያ አዋጅ ... ገጽ ፬ሺ፯፻፶፯

CONTENTS

Proclamation No. 644/2009

Promotion and Reciprocal Protection of Investment Agreement with the Kingdom of Spain Ratification Proclamation Page 4757

አዋጅ ቁጥር ፮፻፵፬/፪ሺ፩

ከስፔን ንጉሣዊ መንግሥት ጋር ኢንቨስትመንትን ለማስፋፋትና ዋስትና ለመስጠት የተደረገውን ስምምነት ለማፅደቅ የወጣ አዋጅ

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥትና በስፔን ንጉሣዊ መንግሥት መካከል ኢንቨስትመንትን ለማስፋፋትና ዋስትና ለመስጠት የባለ-ሁለት ወገን ስምምነት መጋቢት ፮ ቀን ፪ሺ፩ ዓ.ም በማድሪድ የተፈረመ ስለሆነ፣

ስምምነቱ ሥራ ላይ የሚውለው በተዋዋዮቹ ሀገሮች ሕግ መሠረት መጽደቁን የሚያረጋግጡ ሰነዶች በዲፕሎማቲክ አካላት አማካኝነት ልውውጥ ከተደረገ ከ፴ ቀን በኋላ እንደሆነ በስምምነቱ ስለተገለጸ፣

ይህንኑ ስምምነት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሰኔ ፳፫ ቀን ፪ሺ፩ ዓ.ም ባደረገው ስብሰባ ያፀደቀው ስለሆነ፣

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፶፭ (፩) እና (፲፪) መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

PROCLAMATION NO. 644/2009

A PROCLAMATION TO RATIFY THE AGREEMENT ON THE PROMOTION AND RECIPROCAL PROTECTION OF INVESTMENT WITH THE GOVERNMENT OF THE KINGDOM OF SPAIN

WHEREAS, the Agreement on the Promotion and Reciprocal Protection of Investments between the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Kingdom of Spain was signed in Madrid on 17 March 2009;

WHEREAS, it is stipulated in the Agreement that it shall enter into force 30 days after the date of exchange of instruments of ratification through diplomatic channels and receipt of the last notification letter;.

WHEREAS, the House of peoples' Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified the said Agreement at its session held on the 30th day of June, 2009

NOW, THEREFORE, in accordance with Article 55 sub articles (1) and (12) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia it is hereby proclaimed as follows:

Ministry of justice

፩. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "ከስፔን ንጉሣዊ መንግሥት ጋር ኢንቨስትመንትን ለማስፋፋትና ዋስትና ለመስጠት የተደረገውን ስምምነት ለማፅደቅ የወጣ አዋጅ ቁጥር ፮፻፵፬/፪ሺ፩" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

፪. የስምምነቱ መጽደቅ

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በስፔን ንጉሣዊ መንግሥት መካከል ኢንቨስትመንትን ለማስፋፋትና ዋስትና ለመስጠት በስፔን ዋና ከተማ ማድሪድ መጋቢት ፲፯ ቀን ፪ሺ፩ ዓ.ም የተፈረመው ስምምነት በዚህ አዋጅ ፀድቋል።

፫. የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኤጀንሲ ኃላፊነት

የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኤጀንሲ ስምምነቱ በሥራ ላይ እንዲውል ለማድረግ በዚህ አዋጅ ሥልጣን ተሰጥቶታል።

፬. አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

አዲስ አበባ ሐምሌ ፫ ቀን ፪ሺ፩ ዓ.ም

ግርማ ወልደጊዮርጊስ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት

1. Short Title

This Proclamation may be cited as the "Promotion and Reciprocal Protection of Investment Agreement with the Kingdom of Spain Ratification Proclamation No. 644/2009".

2. Ratification of the Agreement

The Investment Promotion and Reciprocal Protection Agreement signed in Madrid on 17 March 2009 between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Kingdom of Spain is hereby ratified.

3. Power of the Ethiopian Investment Agency

The Ethiopian Investment Agency is hereby empowered to implement this Agreement.

4. Effective Date

This Proclamation shall enter into force up on the date of publication in the Federal Negarit Gazeta.

Done at Addis Ababa, this 10th day of July, 2009

GIRMA WOLDEGIORGIS

PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA